# ሰበር ዜና-Breraking News

**Source Tensae Radio**

## የወያኔ ካንጋሮ ፍርድ ቤት በሻለቃ አራጋው ፋይል የተከሰሱት የቅንጂት መሪዎች እራሳቸውን እንዲከላከሉ ወሰነ ፣ ቀጠሮውንም ለግንቦት 30 1999 ዓ.ም ቀጠረ

በትናነትናው እለት ሰኞ  የካቲት 12 /2007 እንደ አውሮፓ አቆጣጠር  ከብዙ ማጉዋተት በሁዋላ የተሰየመው የወያኔ/ኢህአዴግ ካንጋሮ የወንጀል ችሎት ሕገመንግስታዊ ስርአቱን በሃይል ለመናድ ሞክረዋል ብሎ በሶስተኛው የክስ ፋይል ማለትም በነ ሻለቃ አራጋው ሀብታሙ የክስ ፋይል ተከሰው በነበሩት 15 የቅንጂት አመራር አባላት ና ደጋፊዎች ላይ አቃቤ ህግ ተብየው ያቀረበውን የሀሰትና የፈጠራ መረጃዎችን በማድመጥ የሞትና የዕድሜ ልክ እሥራት የሚያስቀጣውን አንቀጽ 238ን በመቀበል ተከሳሾቹ እራሳቸውን እንዲከላከሉ ወስኖአል። ከነዚህም ተከሳሽ የቅንጂት አመራር አባላት ውስጥ ለማመሳሰል በክሱ ተጨምረው የነበሩ 3 ተከሳሾች በነጻ እንዲሰናበቱ ሲወስን  አንዱ ተከሳሽ በሕግ መተላለፍ በ5000 ብር ዋስትና ተለቆ እራሱን ውጭ ሆኖ እንዲክላከል ወሰኗል። አስራ አንዱ የቅንጂት አመራር አባላት የመከላከያ ማስረጃዎቻቸውን ይዘው ለግንቦት 30 ቀን 1999 ዓ.ም እንዲቀርቡ መታዘዙ  የወያኔ/ኢህአዴግ ካንጋሮ ፍርድ ቤት  የታዘዘውን የሚፈጽም ያገዛዙ የፖለቲካ መሳሪያ  ዕንጂ የፍትህ አካል እንዳልሆነ በተገባር መረጋገጡ ታውቆአል። የወያኔ/ኢህአዴግ አገዛዝ ለዓለም ዓቀፉ ሕብረተሰብ ግፊትና ለኢትዮጵያ ሕዝብ ጩኸት ምንም ደንታ የሌለው መሆኑን ደግሞ ደጋግሞ ያስመሰከረበት በመሆኑ በተለይም ይህ የ ፌበሩዋሪ 12.2007 ችሎት በቀጣይነት አገዛዙ ለሚሰጣቸው ውሳኔዎች ጠቃሚ በመሆናቸው ሳንዘናጋ የተጀመረውን የነጻነት ትግል አስተባበሮ መቀጠል ብቸኛ አማራጭ መሆኑን አንድ ጉዳዩን በቅርበት የሚከታተሉት የፖለቲካ ተንታኝ ለትንሳኤ ዜኔ ዘጋቢ ገልጸዋል።